

የነፃነት ፋና ወጊዉ ፣
ወጣቱ መምህር የኔሰዉ ገብሬ

# ጉሮ ወሸባዬ !

ለነፃነት ስትል-ተቃጥለህ ፣
ስትሰዋ ጋይተህ-ከስለህ ፤
እነዳልልህ ጀግና
አልተዘፈነልህ ገና
‹‹ ጉሮ ወሸባዬ
ዝሆን ገዳዬ…›› !
አልቆመልህ ገና-የፍትህ የነፃነት ፣
ግርማ ሞገስ ያለዉ-የወርቅ ያልማዝ ሃዉልት !

ግና እንደነ መም’ሩ
እንደነ አሰፋ ማሩ
የጠመኔ ጀግና
ፋና ወጊ ነህና ፤

ከአራቱ ማ’ዘናት-ከሰሜን ደቡብ ፣
ከምድረ ኢትዮጵያ-ከምስራቅ ም’ራብ ፤

EthioLion.Com

**ይነሳሉ ! እሳት የላሱ ! እሳት የጎረሱ !**
**ሰደድ እሳት የሆኑ ! አራሙቻ የሚያቃጥሉ !!!**

**አርማህን የሚያነሱ !**
**‹‹ አዶ ወሸባዬ... ›› የሚያዘፍኑ !**
**የጀግና መዝሙር የሚዘምሩ !**
**የዴሞክራሲ ዘመን የሚያበስሩ !**
**ይነሳሉ ! - ደቀመዝሙሮችህ !**
**የቁርጥ ቀን ተከታዮችህ !**

**አንተ የኔሰዉ ገብሬ ! - ከጀግናም ጀግና ነህ !**
**ምንጊዜም ህያዉ ነህ ! - አፈር ይቅለልህ !!!**

@@@

**በኢትዮጵያ ፍትህና ነፃነት በመጥፋቱ ፣ ለወገኑ ፋና ወጊ ለመሆን ራሱን በማቃጠል ለተሰዋዉ ለሃያ ዘጠኝ አመቱ ወጣት መምህር**

## ለየኔሰዉ ገብሬ መታሰቢያ

@@@

**አሰፋ ገብረማርያም ተሰማ**
(የቀድሞዉ የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙር ደራሲ)

ህዳር 2004 አ.ም-November 2011
ላስ ቬጋስ - አሜሪካ

**ማሳሰቢያ- እባክዎን ግጥሙን በበኩሎ በልዩ ልዩ መንገድ ያሰራጩት።**

assefagmt@gmail.com

EthioLion.Com